## OUTDOOR EDUCATION (ከክፍል ውጭ ስለሚሰጥ ትምህርት) መረጃ

**የአየር ሁኔታ**

ከክፍል ውጭ የምንሰጠው እንቅስቃሴ በእርጥበታማ እና በቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ ሊሆን ይችላል። ስለሆነም ተማሪዎች ተገቢ የሆነ ልብስ ጋር የግድ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ልጅዎ ለክረምቱ ጊዜ የሚሆን ከበድ ያለ የክረምት ኮት ከሌለው/ከሌላት፣ እባክዎ Ms. McDonald፣ Mrs. Reff ወይም Mrs. McAlarnen ያነጋግሩ።

**ጥንቃቄ/ደንብ**

- ✓ ከትምህርት ቤት ውጭ የሚካሄደው ፕሮግራም የተሣካ እንዲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ትኩረት ለጥንቃቄ መስጠት ነው።
- ✓ የግል ባህርይ እንዲሁ ከጉዞ በፊት ትኩረት ይሰጠዋል። አስቀድሞ ታግደው የነበሩ ተማሪዎች ምናልባት በውጭ ከሚካሄደው ፕሮግራም እንዳይሳተፉ ይጠየቃሉ።
- ✓ እባክዎ በዚህ ፓኬት ውስጥ የተካተተውን ስለ ሚጠበቅ ባህርይ የሚገልጸውን ሽት ገጽ 9 ከተመለከቱት በኋላ ይፈርሙ። ሽቱ ከሌሎች ፎርሞች ጋር መመለስ ይኖርበታል።
  - ▪ መመሪያዎችን ማወቅ እና መከተል የእያንዳዱ ተማሪ ሃላፊነት ነው። መመሪያን በመጣስ የማንኛውንም ተማሪ ደህንነት አደጋ ውስጥ የሚከት በምንም ዓይነት ሁኔታ የሚታለፍ አይሆንም።
  - ▪ ጥንቃቄን በተመለከተ ምንም ዓይነት ማስጠንቀቂያ ወይም ሁለተኛ ዕድል አይኖርም።
  - ▪ ከበድ ላለ ደንብ መተላለፍ ወላጆች ተጠርተው ልጃቸውን ወዲያውኑ እንዲወስዱ ይጠየቃሉ።

**የመነሻ ጊዜ**

ተማሪዎች የጉዞ ሻንጣቸውን በትምህርት ቤት አውቶብስ እንዲያመጡ MCPS አይፈቅድም።

- ☐ እባክዎ ልጅዎ እና የልጅዎ የጉዞ ሻንጣዎች ጠዋት በ8፡00 a.m. ሰዓት ትምህርት ቤት (የMs. McDonald's ተማሪዎች) ሰኞ በ ኖቬምበር 17፣ 2008 እ.ኤ.አ ወይም (የMs. Abiodun's ተማሪዎች) ረቡዕ ኖቬምበር 19፣ 2008 እ.ኤ.አ እንዲደርሱ ዝግጅት ያድርጉ።
  - o ልጅዎ ለጉዞ ሁለት ሻንጣዎች ብቻ ሊኖሩት ይገባል። አንድ ሻንጣ ወይም የጉዞ ቦርሳ እና አንድ የመኝታ ከረጢት (እስሊፒንግ ባግ) ሲሆን ውሃ በማያስገባ ፕላስቲክ መሸፈኛ በጥንቃቄ መጠቅለል ይኖርበታል።
  - o በልጅዎ የጉዞ ሻንጣ ላይ በግልጽ እንዲታይ ሆኖ የመጠሪያ እና የቤተሰብ መጠሪያ ስም መጻፍ ይኖርበታል።
- ☐ እያንዳንዱ ተማሪ ለመጀመሪያ ቀን Outdoor Ed የሚሆን ምሳ ያስፈልገዋል። ምሳው በሻንጣ ውስጥ መታሸግ አይኖርበትም።
  - o ሁሉም የምሳ ዓይነቶች የግድ ከተቀም በኋላ በሚጣሉ ቀለል ባሉ መያዣዎች መሆን ይኖርባቸዋል። በግልጽ እንዲታይ ሆኖ የልጅዎ የመጠሪያ እና የቤተሰብ መጠሪያ ስም በምሳ ዕቃው ላይ መጻፉን እርግጠኛ ይሁኑ። የመጠጥ አቅርቦት ይኖራል።

**<u>የመመለሻ ቀን</u>**

- ☐ በግምት 1፡15 p.m. ከሰዓት በኋላ ሲሆን ተማሪዎች ወደ Newport Mill Middle School ይመለሳሉ። (የMs. McDonald's ተማሪዎች) ረቡዕ ኖቬምበር 19፣ 2008 እ.ኤ.አ. ወይም (የMs. Abiodun's ተማሪዎች) አርብ, ኖቬምበር 21, 2008 ይሆናል።
  - o አውቶብሱ አራግፎ ከጨረሰ በኋላ የስድስተኛ ክፍል ተማሪዎች ከእነ እቃቸው ወዲያውኑ ወደየ ቤታቸው እንዲሄዱ ይደረጋሉ።
  - o ልጅዎን በዚህ ሰዓት ለመቀበል የመጓጓዣ አገልግሎት ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው።
  - o ስለ ልጅዎ ጉዞ መፍቀድዎን ከሚያረጋግጡበት ፎርም ጋር ማን ወደ ት/ቤት እንደሚያመጣው እና ወደ ቤት እንደሚመልሰው በግልጽ ማስቀመጥዎንም እባክዎ እርግጠኛ ይሁኑ።

  እንደገና፣ ለደህንነት ሲባል ተማሪዎች በመደበኛ የት/ቤት አውቶቡስ ላይ ሻንጣቸውን መጫን አይፈቀድላቸውም። ተማሪዎች የከሰዓት በኋላውን አውቶቡስ እንዲጠብቁ አይፈቀድላቸውም።

**<u>ለምንድ ነው የMCPS የOUTDOOR ED ተሳትፎ የሚበረታታው?</u>**

የMCPS ስድስተኛ ክፍል Outdoor Education ከክፍል ውጭ ለሦሥት የቀን እና ለሁለት ቀን የአዳር፣ ስሜትን እያነቃቃ ልምድ የሚቀስሙበት ፕሮግራም ሲሆን፣ የዚህ ፕሮግራም ዓላማዎች፡

- ✓ ተማሪዎችን ስለ አካባቢ ተፈጥሮ ግንዛቤ፣ ዕውቀት፣ አድናቆት እና ተቆርቋሪነት እንዲኖራቸው ለማዘጋጀት።
- ✓ ተማሪዎችን ስለ አካባቢ ተፈጥሮ ግንዛቤ፣ከተለያየ ልምድ በመማር አዎንታዊ ዝንባሌያቸውን እንዲያሳድጉ ለማነቃቃት።
- ✓ ተማሪዎችን ብዙ ቀጥተኛ ልምዶችን በሳይንሳዊ ሂደቶች፤ ለምሳሌ ተደጋጋሚ ዕይታዎች፤ በመለካት፤ በመከፋፈል፤መላ በመምታት እና በመተንበይ እንዲጠቀሙ ለማዘጋጀት።
- ✓ በክፍል ዉስጥ የተገኘውን ዕዉቀት እና ችሎታ ከክፍል ዉጪ በተጨባጭ ሁኔታዎች እንዲያውሉት በማድረግ የተማሪዎችን የትምህርት ፕሮግራም በበለጠ ትርጉም የሚሰጥ ለማድረግ።
- ✓ ተማሪዎችን በዲሞክራሲ መኖርን እና የጋራ ደህንነት ለመጠበቅ ሐላፊነት እንዲሰማቸው እንዲማሩ መርዳት። በወጣቶች እና በህጻናት መካከል ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት ለማሻሻል።
- ✓ ስለአካባቢ ሐላፊነት ቀስ በቀስ እንዲሰማቸው እና ለዚህም የሚገባውን አዎንታዊ ምላሽ እንዲያደርጉ ለማበረታታት።

ይህ መረጃ ጠቃሚ እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን። ወላጆች እና ተማሪዎች አንድ ላይ ሆነው ይሄንን መረጃ በጥንቃቄ ማንበብ ይኖርባቸዋል። ይህ ዕድል ተማሪዎች በወላጆቻቸው እና በመምራን በመደገፍ ለራሳቸው ሐላፊነት የሚወስዱበት እድግ በጣም ጥሩ አጋጣሚ ነው። ሌላ ተጨማሪ የምንረዳ ሆነን ከተገኘን፤ እባክዎ በስልክ ቁጥር 301-929-2244 ይደውሉልን።

# ለውጭ ትምህርት መምጣት ያለባቸው ነገሮች

**መኝታ**

- ☐ አንሶላዎች እና የብርድ ልብስ ወይም አንሶላ እና የመኝታ ከረጢት
- ☐ ትራስ

**የንፅህና መገልገያዎች**

- ☐ የጥርስ ሳሙና እና የጥርስ ቡሩሽ
- ☐ ሳሙና ከነ ማስቀመጫው (አነስተኛ የፕላስቲክ ባለዚፕ ቦርሳ በጣም ይመረጣል።)
- ☐ የባኞ ቤት ፎጣ
- ☐ ቡሩሽ
- ☐ ሻምፑ/ፈሳሽ ሳሙና
- ☐ የሰውነት ጠረንን ወደ ጥሩ መዓዛ ለወለወጥ የሚያገለግል ሽቶ

**አልባሳት፣** (አልባሳት ላይ ስም ይፃፉ፣ ለውጭ የሰውነት እንቅስቃሴ አመቺ እና ተስማሚ የሆነ ልብስ ብቻ አምጡ። ከጥቅም ውጭ ለሚሆን ነገር አዲስ ከመግዛት ይቆጠቡ።)

- ☐ የመኝታ ልብስ
- ☐ የውስጥ ልብስ
- ☐ ካልሲዎች (5 ጥንድ)
- ☐ ሁለት ጂንስ ሱሬዎች ወይም በቀላሉ የሚጠለቁ ሰውነትን በሚያልብ ጊዜ ለመለበስ የሚመቹ ሱሪዎች
- ☐ ሙቀት የሚሰጡ እጅጌ ሙሉ ሸሚዞች ወይም ሹራቦች (ኖቬምበር ስለሆነ እና ውጭ ብዙ ስለምንቆይ።)
- ☐ ቲ-ሸርት
- ☐ ሁለት ጠንከር ያሉ ጫማዎች (እስኒከር ተመራጭ ነው።)

**የውጭ ልብስ**

- ☐ ለሙቀት የሚሆን ጃኬት/ኮት
- ☐ የፀጉር ቆብ ባርኔጣ ወይም ትንሽ ሻሽ
- ☐ የዝናብ ልብስ ወይም ትልቅ የቆሻሻ መያዣ ላስቲክ (እኛ እናቀርባለን)

**የማያስገድዱ/ቢኖሩ የሚመረጡ**

- ☐ የፕላስቲክ ውሃ መያዣ
- ☐ ለከንፈር ውበት እና ደህንነት የሚቀባ
- ☐ ለቆሸሸ ልብስ ማጠራቀሚያ የሚሆን ትልቅ የላስቲክ መያዣ

**ወደ ካምፕ ይዞ መምጣት የማይፈቀዱ ዕቃዎች**

- ☠ በኪስ የሚያዝ ሴንጢ/ቢላዋ
- ☠ ነጠላ ጫማ
- ☠ የፀጉር ማድረቂያ
- ☠ የሚጠጣ፣ ማስቲካ፣ እስናክ ወይም ምግብ
- ☠ ማንኛውም ኤሌክትሮኒክስ
- ☠ ክብሪት ወይም ላይተር
- ☠ ገንዘብ

ሌሎች ዕቃዎች በማንኛውም ጊዜ ወደ ት/ቤት ማምጣት የማይፈቀዱ።